**እንጉርጉሮ ለትግራይ ተሰቃይዎች**
**(ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ)**

***(በአዲስአበባ ሲለምኑ÷ሲንገላቱም ላየኋቸው የትግራይ ሰዎች)***

**ሴቶቹ÷ ጨፋ ሹሩባቸው ግጥም እንዳለ÷**
**መስቀላቸው ታትሞ በግንባራቸው÷**
**አድፎ÷ ተበጫጭቆ ነጠላ÷ ቀሚሳቸው÷**
**ተሰነጣጥቆ ባዶ እግራቸው÷**
**ወንዶቹም በእራፊ ሸማ**
**ሃፍረታቸውን እንደነገሩ ሸፍነው÷**
**ካገራቸው ድረስ በተመረኮዙት ዱላ**
**ከውሾች እየታገሉ÷ ኩራታቸውን አፍነው÷**
**ሁላቸውም የዘመናት ስቃይና እንግልት÷**
**እንደ መጽሐፍ እየተነበበ ከፊታቸው÷**
**እኛውና የትግራይ ባልቴቶች÷ አዛውንቶች÷**
**እኛውና ማቲዎች ከነናቶቻቸው እየታከታቸው**
**በማያውቁት ቋንቋ ዋይ!ዋይ! ይላሉ፤**
**የመከራ ውርጅብኝ እየመታቸው÷**
**በችጋር እየተጠበሱ ይለምናሉ፤**
**በጠኔ እየተቆሉ÷በአዲስአበባ በራፎች**
**ክብራቸው ተገፎ ጉርሻ ይማጠናሉ::**

**መከለያ ጎጆ አጥተው ወድቀዋል**
**ያለፍራሽ÷ ያለብርድልብስ እመሬት ላይ÷**
**በውርጭ÷ በዝናብ÷ በጎርፍ ውስጥ÷**
**ባገራቸው ታዛ ተነፍገው እንደ ኮብላይ::**

**ሺ ላም ታለበ ሲባል÷**
**ወተት በገልም ያልደረሳቸው÷**
**ሺ ሰንጋ ተጣለ ሲባል÷**
**ቅርጫ ቀራጭ ሙዳ ሥጋ የነሳቸው÷**
**ትግራይ አበበች ሲባል÷**
**መጠውለግ ሆኖ እጣቸው÷**
**ትግራይ ቁንጣን ያዛት ሲባል÷**
**እነሱን ራብ አመንምኗቸው ያለቅጣቸው÷**
**ከትውልድ ቀያቸው ነቅሎአቸው÷**
**ሞት ለከርሰ-ምድር እስኪሰጣቸው÷ ስማቸው**
**ተሸቅጦበት÷ ተብለው አሉበት በሌሉበት÷**
**ስማቸው ጦስ'ንጂ ቤሳቤስቲ ያላተረፋቸው÷**
**ሰብዕናቸው ተገስሶ÷ ኩራታቸው ተረግጦ÷**
**እኛውና አረጋውያን የሰው ፊት እየገረፋቸው!**
**እኛው በማረፊያቸው ወቅት እየባዘኑ÷ እኛውና**
**የተገፉት÷ እየተንከላወሱ በመጦሪያቸው ሰዓት÷**
**ከለበሱት ቡትቶ በቀር ቅርስ አጥተው÷እኛው**
**ኢትዮጵያዊ እመው÷ አበው÷ ወርዶባቸው መአት!**
**እኛውም እመንገድ ላይ እምቡጥ ሕጻናት÷**
**በትምህርት ያልዋሉ÷ልጅነታቸው አጥቶ ቅጥ÷ ስርዓት::**

ወየው! ኧረ ሰወየው! ምን ይበል አክሱማይ
የግብጹ ፈርያን ራሚሱ÷ የኢትዮጵያ ባል÷
ያፍሪካ አሳዳሪ÷ የእስያ ጌታ÷ያረብያ አባብያ÷
ያስራደው ናቡከደኖፀርን በቁጣው ነበልባል?

ያነጻው አክሱምን በሥሙ
የገነባው ህንጻ÷ ሃውልት÷
እናንተ እሜዳ እንዳታድሩ÷
እናንት እንዲኖራችሁ ርሥት÷ ጉልት፡፡

እውነት ምን ይበል አክሱማይ÷
ባለም ተቆላምጦ “ያለምአባት” ተብሎ÷
ስለ ርሕራሄው÷ ስለፍትሁ ካለም ዳርቻ ህዝቡ
የገባለት ከ'ስያ÷ ካፍሪካ÷ ከጨቋኝ ገዦቹ÷ ኮብሎ?

በውን ምን ይላል ደጉ÷ ትልቁ አክሱማይ÷
ባዕዳን ወደሱ ሲጎርፉ ሽተው ፍትህ÷ ጥጋት÷
ልጆቹ በገዛ ሃገራቸው ተሰደው÷ ቢያያቸው
ተርበው÷ ታርዘው÷ መሬት አጥተው አንዲት ጋት?

ምነዋ ዛሬ ሲባል ትግራይ ህንጻዎችን
ከመረች÷ አእላፍ ሰማይ-ቧጣጮች ገነባች÷
ምነዋ እናንተን እሜዳ አሳድራ
በብርድ አቆራፍዳ ደም አስነባች?

ምነዋ ሲባል ትግራይ ቶጀረች÷
ያልባሳት ፋብሪካዎች ደረደረች÷
እናንተን ርቃናችሁን ሰዳ÷ ገመናችሁን
አጋልጣ አዋርዳ÷ መለመላችሁን አሳደረች?

ምነዋ ሲባል ትግራይ÷ ጭንጫውን÷
በርሃውን አለምልማ አረነጎደች÷
እናንተን በጠኔ አመንምና÷ አጽማችሁን
አስቆጥራ÷ ዐይናችሁን አስጎደጎደች?

“የትግራይ ነጻ-አውጪ” ተብሎ በስማችሁ
ደም የጎረፈ÷ ለድሎታችሁ አልነበር 'ንዴ?
የትግራይ ልጆች ምነው የሚላስ አጣችሁ?
ያሁሉ የተገባላችሁ ቃል ተረሳ ባንዴ?

ከገዢዎቹ÷ ከባለጊዜዎቹ ጋር
“አባሪዎች ናቸው፤'
ብሎ ህዝቡ “ከቶ ይሆን ያባርር÷ ይኮንናቸው?
“ወይስ አመዛዝኖ
“ይቆም ከጎናቸው?”
ብዬ ባይ ተከታትዬአችሁ÷
የህዝቡ ርህራሄ ወጣ ተፈልፍሎ፤
ህዝቡአርቆ-አሳቢ ሆኖ÷
መቼ ይጨክናል በስሜት ገንፍሎ

ድሃ ወገኖቼ ተሰቃዩ ብሎ÷ ዐየሁ
ሲዘከራችሁ ያለችውን አካፍሎ።

እናንተንና የኢትዮጵያን የኔ ብጤዎች
እስቲ ልጠይቃችሁ÷ መልስ ስጡኝ በሞቴ÷
በውን እናንተም ለመኖር ትጓጓላችሁ
አገር አለኝ ብላችሁ? እኔስ ፈቷል ሃሞቴ
የናንተን ሰቆቃ አጢኜ። ባንዲራዋ÷ አፈሯ
እኮ ምንድነች ለናንተ? ለኢትዮጵያ በውን
ትሞቱላታላችሁ? ነፃነት÷ አገር÷ ህዝብ አለኝ
ብላችሁ ከልባችሁ ታወራላችሁ? አለኝታውን
አገርን ወዳችሁ÷ እንደ ዘሮቻችሁ ሆናችሁ
ትከተላላችሁ አራያቸውን የእመው÷ ያበውን?

እሱስ ደኸየሁ ብሎ
ሰው አገሩን አይጠላም።
እሱስ አልደላኝም ብሎ ሰው ከክብሩ÷
ከቶም ከሰንደቃላማው አይጣላም።

እሱስ ልመናም ሆነ ቀብር÷
ጥንትምኮ ባገር ነው የሚያምር።
ምጽዋት የሚገኝም ደግ ህዝብ ሲኖር ነው÷
አዛኝ ሲገኝም ነው ርጥባን የሚሰምር።

ያው እንደናንተው ያጣው የነጣው ነው
ያለው ርህራሄ÷ የሚያደርግም ትሩፋት።
ያ በስማችሁ ከብሮ÷ናጥጦ ዛሬ ጆሮውን ቢቆርጡት
የማይሰማውማ÷ ረስቷል ርሃብ÷ የሰው ፊትም ግርፋት።

ህዝበ–ኢትዮጵያማ ደግነው÷
ትህትና÷ ርህራሄ የተካነው።
"የኔቢጤ" ይላል በትህትና ለማኙን
ራሱን ከለማኝ እየወገነው።

እሱስ እናንተና መሰሎቻችሁ አይደላችሁ
ድሮስ በኢትዮጵያ ፍቅር ነዳችሁ÷እንዳያት
ምኾላት÷ ሽማታችሁ÷ አንገታችሁን ለሰይፍ
የምትዳርጉላት? የደላውማ መች ዞሮ ሲያያት?
እናንተማ ጦብያ ብቻ ናት አገራችሁ። በዳያችሁ
ግን ሁሉ–አገሩነው። ሊግጣት ነው የሚሰነጣጥራት
ጦብያን። ግጧት ግጧትም ሲቀር አጥንቷ ብቻ÷
ይፈተለካል÷ ሳይሳሳ እላቂዋን ሲያሽቀነጥራት።

የኧላ ኧላማ÷ የማታ÷ ማታማ
ይነጋል ሌሊቱ÷ አይቀርም በመጨለም።
ፍትሕ÷ ቅጣት÷ ካሳ ግን÷ ወዲያው አይፈጸምም
ሸር÷ ዕብሪት÷ ጭካኔ÷ በሰረረው በዚህ ዓለም÷
ሁሌ የግፍ ብድር ፈጥኖ አይመለስም፤
እውነቱም እያደር'ንጂ÷ ቶሎ 'ሚጠራ አደለም።

ሥለዚህ መሸቶባችሁአል እናንተ!
ገና ፍርድ ተገኝቶ እንደሰው እስክትመገቡ፥
ገና ፍትህ ተከስቶ እንደ ሰው እስክትለብሱ፥
ሕይወታችሁ ያከትማል ገና እቤት እስክትገቡ።

እናንተማ ናወዛችሁ ከትግራይ እስከ ሸዋ፥
ተስፋ ሳትቆርጡ አዲስ ህይወት ፍለጋ።
ዳሩ ህይወታችሁ አልሆነም 'ንጂ ፍክ አበባ።
አ'ለቅም ብሏችሁ የተጠናወታችሁ ጥውለጋ።
ወይቦ የጠወለገ ይደርቃል 'ንጂ፥
ዳግም ታድሶ ስለማይሆን ለጋ።

እንግዲህ እግዜር ይሁናችሁ ዘመዶቼ። እሱው
ይማለዳችሁ ወገኖቼ። ለጊዜው አልሰምርላችሁ
ብሎ ዕድላችሁ፥ የምድሩንስ አጣችሁታል።
ከሃሊው በቸርነቱ የሰማዩን ያሳምርላችሁ።

እኤአግንቦት5ቀን1999